# የአፄ ዮሐንስ የመጨረሻ ቀናት

## (ከዛሬ 127 ዓመታት በፊት)

ጆሴፍ ኦርዋልድ እንደታዘበው

ሻለቃ ኢ. አር. ዊንጌት እንደዘገበው

(Ten Year's in Captinvity in the Mahdis' Camp 1892)

<u>በክፍለጽዮን ማሞ</u> (ትርጉም)

### <u>ዘመቻ ተክለሃይማኖት</u>

የእንግሊዝን የበላይነት ለመቋቋምና ከረር ያለ ሃይማኖታዊ የፖለቲካ ሥርዓት ለመመሥረት በ1870ዎቹ በ ሱዳን አ ንድ ጠ ንካራ መ ንግሥት በ አልማህዲ መሪነ ት ተቋቋመ። ንቅናቄ ው ግብጽን በመቆጣጠር የናይልን ወንዝ እስከምንጩ ድረስ ለመያዝ በመስፋፋት ላይ ለነበሩት እንግሊዞች ትልቅ ስጋት ከመሆኑም በላይ ለኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት አፄ ዮሐንስ እና ለአማራው ንጉሥ ተክለሃይማኖት የእግር እሳት ሆነ። በመሪው በማህዲ ስም ማህዲዝም (አንዳንድ ጊዜም ድርቡሽ) እየተባለ የሚጠራው ይህ እስላማዊ መንግሥትን በወታደራዊ ኃይል ጭምር በአካባቢው ለመገንባት የተጀመረው ንቅናቄ ካርቱምን በመክበብና በማጥቃት እዚያ የነበረውን የእንግሊዝ ባለሥልጣን በመግደል፣ እንደዚሁም የኢትዮጵያን ሰሜናዊ ምዕራብ አካባቢዎች በየጊዜው በማጥቃት ግልጽ ጦርነት አወጀ።

በተለይ ገላባት ላይ ሴቶችና ህፃናትን ጨምሮ በርካታ የእንግሊዝ ወታደሮች በደርቡሾች ተከበው ለረሃብና ለውኃ ጥም በመዳረጋቸው የእንግሊዝ መንግሥት የአፄ ዮሐንስን እርዳታ በመጠየቅ ለእልቂት የተደረገትን የግብጽና የእንግሊዝ ዜጎች እንዲያስለቅቁላቸውና እንግሊዝም የኢጣሊያ በቀይ ባህርና በዛሬዋ ኤርትራ ስታደርግ የነበረውን ወረራ አቁማ የኢትዮጵያን ምድር ለቅቃ እንድትወጣ እንዲያደርጉ አድዋ ላይ ውል ገቡ።

የኢትዮጵያ መንግሥት በዚሁ በአድዋ ስምምነት መሠረት ወታደሮቹን በመላክ የእንግሊዝን ዜጎች በረሃ ላይ በመክበብ እልቂታቸውን ሲጠብቅ የነበረውን የድርቡሽ ኃይል በመደምሰስ ካስለቀቀ በኋላ በጎንደር በኩል ምፅዋ ድረስ በሰላም ሸኘ። ደርቡሾች የዚህ የገላባትን ጥቃት ለመመለስ ሌላ ዝግጅት በማድረግ ከተማዋን ለመቆጣጠር ጊዜ መጠበቃቸው አልቀረም። ንጉሥ ተክለሃይማትም ደርቡሽ ሽንፈትን በፀጋ እንደማይቀበል ስለሚያውቁ ዝግጅታቸውን አጠናከሩ። ብዙም ሳይቆይ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የድርቡሽ ሠራዊት ለውጊያ የተሰናዳ መሆኑ መረጃ ደረሳቸው።

ንጉሥ ተክለሃይማኖት 20,000 ፈረሰኞችን ጨምሮ ወደ 100,000 የሚጠጋ ሠራዊት መርተው ማህዲስቶችን ለመግጠም ጋራ ሽንተረሩን አቋርጠው ገላባት (መተማ) ወረዱ። የማህዲዝምን ኃይል የተሞላበት አገዛዝ በመቃወም የካዱ በርካታ ታላላቅ የጦር መሪዎች የንጉሥ ተክለሃይማኖትን ሠራዊት ተቀላቅለዋል። የገላባትን ምሽግ አጠናክሮ የያዘው ዋድ አርባብ የተባለው የጦር አዛዥ የተክለሃይማኖትን

ዘመቻ በሰላዮች አማካይነት ይከታተልና በየጊዜውም መረጃ ይደርሰው ነበር። ይህ የውጊያውን መጀመር በንቃት ይጠባበቅ የነበረ የዋድ አርባብ ጦር የውጊያ ልምድን ያዳበሩ 16,000 ተዋጊዎችን ያደራጀ ኃይል ነበር።

የንጉሡ ሠራዊት በተለይ ፈረሰኛው ምድብ በሙሉ ወኔና ጅግንነት የድርቡሽን ምሽግ ጥሶ መግባት ጀመረ። ድርቡሾች ወደ ኋላ ማፈግፈግ፣ ሀበሾቹም ማጥቃትና ድል በድል ላይ መጎናፀፍ ቀጠሉ። የገላባት ከተማ በእሳት ነደደች። በበረሃማው አውሎ ነፋስ የተባባሰው የእሳት ንዳድ እየዘለለ የድርቡሾቹን የጥይት መጋዘን አቃጠለ። በቃጠሎው የ ፈንዳው የጥይት ባሩድ በሽሽት ላይ የነበረውን የማህዲስት ጦር እየተከታተለ አነደደው። የንጉሥ ተክሃይማኖት ሠራዊት ከጦርነቱ ወላፈን የተረፉትን ሴቶችና ህፃናት እንዲሁም ሰላማዊ የሱዳን ዜጎች በምርኮ በመሰብሰብ ይዟቸው ሄደ። ገላባትን ምድረ-በዳ በማድረግ አገሩ ገባ።

ይሁን እንጂ ከዚህ ውጊያም በኋላ ድርቡሾች ወጣ ገባ እያሉ በንፁሃን ኢትዮጵያውያን እንዲሁም በቤት ንብረታቸው ላይ ወረራ መፈፀማቸውን አላቆሙም።

ከአልማህዲ እረፍት በኋላ የድርቡሽ መንግሥት መሪ የነበረው ኸሊፋ አብዱላሂ በሐምሌ ወር 1880 ዓ.ም. (ጁላይ 1887 እ.ኤ.አ.) ለአፄ ዮሐንስ አንድ ደብዳቤ ላከ። ደብዳቤው የሰላም ጥሪ ያዘለ ሲሆን በኢትዮጵያና በሱዳን መንግሥታት መካከል እርቀ-ሰላም እንዲወረድ አፄ ዮሐንስ የሚከተሉትን ሦስት ጉዳዮች እንዲፈፀሙ በቅድመ ሁኔታነት ይጠይቃል።

አንደኛ፡- አፄ ዮሐንስ እስልምናን እንዲቀበሉ፣

ሁለተኛ፡- በንጉሥ ተክለሃይማኖት ሠራዊት የተማረኩት ሴቶችና ህፃናት እንዲመለሱ፣

ሦስተኛ፡- የማህዲ አገዛዝን በመቃወም ከኢትዮጵያ ጎን የተሰለፉት ዋና ዋና የጦር አዛገሮች ተላልፈው እንዲሰጡ።

አፄ ዮሐንስ ለደብዳቤው ምላሽ ከመስጠት ይልቅ ዝምታን መረጡ።

ወራት እንደ ቀናት ነጎዱ። ኸሊፋ አብዱላሂ የገላባትን ጥቃት ለመበቀል ከኢትዮጵያ ጋር ጦርነት መግጠም ጊዜው ደርሶ እንደሆነ ጦር አለቆቹን በመሰብሰብ ምክክር ጀመረ። ውሳኔው ግልጽ ነበር፤ ጦርነቱ ሳይውል ሳያድር እንዲጀመር አብዛኞቹ የድርቡሽ ጦር አዛገሮች ተስማሙ። ይህ በእንዲህ እንዳለ ንጉሥ ተክለሃይማኖት ግዙፍ የጦርነት ዝግጅት በማድረግ ላይ መሆናቸው በድርቡሾች ሰፈር ተሰማ። ይህ ዜና ኸሊፍ አብዱላሂ ለዘመቻው ይበልጥ ቆርጦ እንዲነሳ አደረገው። የእህቱን ልጅ አቡ አንጋን የዘመቻው መሪ አድርጎ ሾመው። ኸሊፋ ሠራዊቱን ባርኮ ሲሸኝ ከፍ ባለ ድምፅ እያንዳንዱ የማህዲስት ተዋጊ ለማህዲ እምነት ካላአንዳች ፍርሃት እንዲዋደቅ ያደረገው ንግግር ሠራዊቱን በጠቅላላ በእንባ አለበሰው። ከጥንት-ታሪክ ጀምሮ በወታደራዊ ኃይሏ ከግብጽ ይልቅ ጎልታ የምትታየውን ኢትዮጵያን እንዲዘህ በመሰለ ጦርነት ማሸነፍ የተለመደ ባለመሆኑ ኸሊፋው እየደጋገመ ልብን በሚቀሰቅስ ንግግሩ ሥራዊቱ በቁርጠኝነት እንዲዋጋ ተማፀነ።

የውጊያ አመራሩን ከኸሊፋ የተረከበው አቡ አንጋ 81,000 ተዋጊዎችን በመምራት ሀገሪቱን ወረረ። የድርቡሽ ጦር የኢትዮጵያን ጋራና ሸንተረር በማቆራረጥ በርካቶች በድካም መንገድ ላይ የቀሩበትን ረዥም

ጉዞ ለመንዝ የሰሜን ምዕራብ ወረዳዎችን በቁጥጥሩ ሥር አደረገ። ፈጣሪ ለኢትዮጵያ የሰጠውን በረከት በየመንገዱ ወረረ። ሱዳኖች ምን ጊዜም እንደ ዕፁብ ድንቅ ምድር የሚያዩአትን ሀገር በተፈጥሮ ፀጋዋና በመልካምነቷ ይበልጥ እየተገረሙ የገበሬውን ሴት፣ ሚስትና ንብረት ይፈሩ።

የንጉሥ ተክለሃይማኖት ሠራዊት ደምቢያ (ሳር ውኃ) ላይ መሸጉ። ደምቢያ ከመተማ (ከገላባት) በስተምሥራቅ በስድስት ቀናት የእግር መንገድ ርቀት ላይ ይገኛል። ተክለሃይማኖት ከደምቢያ ምሽጋቸው ላይ ሆነው የአቡ አንጋን ጦር መምጣት በትዕግስት ይጠባበቃሉ።

አቡ አንጋ ደምቢያ ላይ እንደደረሰ ሠራዊቱን ለውጊያ በማነቃቃት፣ በዋና ዋና የጦር አዛዦች የአራት ማዕዘን ዙሪያ መሀል ሆኖ ውጊያውን ለማስጀመር ተቃርቧል። ውጊያው ተጀመረ። ድርቡሾች ወደ ሀበሾቹ ሠፈር መገስገስ ጀመረ። የሀበሾቹ ሠራዊት ብዛት እንኳን በጦርነት በዓይን እይታም የሚያልቅ አይመስልም።

የንጉሥ ተክለሃይማኖት ሠራዊት ግንባሩን ለአረር ደረቱን ለጦር አጋልጦ እየሰጠ የመጣበትን ወራሪ ማጥቃት ጀመረ። በድፍረት ክብራቸውን ለማዋረድ የተነሳባቸውን ጠላት ለመመከት የአንበሳ ሞት ለመሞት በጀግንነት ተዋደቁ፤ በተለይ ፈረሰኛው ተዋጊ ለነፍሱ ሳይሳሳ የድርቡሽን ምሽግ መሀል ለመሀል ሰንጥቆ በመግባት አርበኝነቱን አስመሰከረ።

ሆኖም ድርቡሾች በተለይ ትኹሪሮቹ (ጥቋቁሮቹ) ተዋጊዎች እንደወትሮው ሁሉ ልዩ የውጊያ ስልታቸውን አሳዩ። በታጠቁት የጦር መሣሪያ የኢትዮጵያዊያንን ደም አፈሰሱ። በዚህ ያልተበገሩት ሀበሾች ግን የድርቡሽን ጠንካራ ምሽግ ለመስበር አሁንም ወደፊት እያሉ ተዋጉ። ዞሮ ዞሮ የድርቡሾች የበላይነት እርግጥ እየሆነ ሄደ። የንጉሡ ሠራዊት በድርቡሾች እጅ ገብተው ስቃይና ውርደትን ከማየት ጦርነቱ ማብቃቱ እርግጥ ሆኖም እያለ እስከመጨረሻው ድረስ በያዙት ሁሉ እየገደሉ መሞትን መረጡ።

በደምቢያ ጦርነት ድርቡሾች ሊያሸንፉ የቻሉባቸው ሦስት ዋና ምክንያቶችን መጥቀስ ይቻላል።

አንደኛ፡- ጠንካራ ወታደራዊ ዲሲፕሊን ማለትም የእርስ በእርስ መናበብና ቅንጅት፣

ሁለተኛ፡- የሠራዊቱ አሰላለፍ (ስትራቴጂ) የበላይነት፣

ሦስተኛ፡- የተሻለ የጦር መሣሪያ፣

በዚህ ዐውደ-ውጊያ አብዛኞቹ የንጉሥ ተክለሃይማኖት ምርጥ የጦር አዛዦች ተሰውተዋል። በድርቡሾች እጅ ከተማረኩት መካከል ወደገላባት የተወሰዱት ወንድ ልጃቸው ይገኙበታል።

ከድሉ በኋላ ድርቡሾች የንጉሡን የጦር ሠፈር ወረሩት። በርካታ የጦር ሜዳ ድንኳኖች፣ የጋማ ከብቶች፣ እና ሁለት መድፎች ከእጃቸው ገቡ። የጋማ ከብቶቹ ብዛት ከቁጥር በላይ ስለነበረ እነሱን እያነዱ የስድስት ቀናት ጉዞ ከሚጓዙ እንስሶቹን አንገታቸውን በመቁረጥና በማቃጠል ግፍ ፈጸሙ።

ወደ ቀደምትዋ የኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ ጎንደር የሚወስደው መንገድ አሁን ለድርቡሽ ሠራዊት ወለል ብሎ ታየው። አቡ አንጋ ጎንደር ላይ ከፍተኛ መጠን ያለው ሀብትና ንብረት አገኛለሁ ብሎ በጥድፊያ ገሰገሰ። ከጦር ሜዳው የ50 ኪሎ ሜትር ያህል ርቀት ተጉዞ ጎንደር የገባው የድርቡሽ ጦር ስንጥር ሳያስቀር ከተማዋን መዘበረ። ከዝርፊያው በኋላ ከተማዋን በእሳት አቃጠለ። ቤተክርስቲያኖች

ተዘረፉ፣ በእሳትም ጋዩ። ካህናትም ከየተደበቁበት እየተያዙ ከጣሪያ ላይ እየተወረወሩ ተገደሉ። የጎነደርና የአካባቢዋ ነዋሪ ሕዝብ ተጨፈጨፈ። በመቶዎች የሚቆጠሩ ሴቶችና ህፃናት ለባርነት ተጋዙ።

## ሰሚ ያጣ የሰላም ጥሪ

አቡ አንጋ በንጉሥ ተክለሃይማኖ ላይ ያገኘውን ድል ተከትሎ በኢትዮጵያ ሰሜን ምዕራብ ወረዳዎች የሚኖሩት ማህበረሰቦች እስልምናን ተቀበሉ። አቡ አንጋ ውጊያ የተካሄደባቸውን ሥፍራዎች ካረጋጋ በኂላ ከሊፋ አብዱላሂ ወደነበረበት ጊዜያዊ የአምድሩማን ቤተመንግሥት ጉዞ ጀመረ። በዚህ ጊዜ ነበር ከሊፋ ከኢትዮጵያው ንጉሥ-ነገሥት በብራና ላይ በአማርኛ ቋንቋ የተጻፈ ደብዳቤ የደረሰው። አምድሩማን ውስጥ ይኖሩ ከነበሩት ኢትዮጵያውያን ዓረብኛን የሚያቀላጥፉ ሁለት ሰዎች ለአስተርጓሚነት ተጠርተው ቀረቡ።

ለድርቡሹ መሪ ከአፄ ዮሐንስ የተላከው ደብዳቤ የሚከተለውን ያዘለ ነበር።

> *ይድረስ ለወንድሜ ኸሊፋ አብዱላሂ፤ ለጤናዎ እንደምን ሰንብተዋል። በሁለታችንም ሕዝቦች መሀል የገባውን ጠብ ለማብረድና ሚዛናዊ እርቀ-ሰላም ለማድረግ ከልብ የፈለቀ ፍላጎቴን ልገልፅልዎት እወዳለሁ።*
>
> *የሁለቱ አገሮች ሕዝቦች ከአንድ ከህም የዘር ሐረግ የመጣን ወንድማማቾች ነን። በአሁኑ ጊዜ ማቆሚያቸው የት እንደሆነ የማይታወቅ ፈረንጆች እርስዎንም እኔንም እየከበቡን ነው። ፍጥነታቸውም ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ ይገኛል። የኢትዮጵያና የሱዳን ሕዝቦች ወንድማማችነትና ጉርብትና እነዚህን ባዕዳን ለመከላከል እንጂ በእርስ በእርስ ጦርነት ልናውለው አይገባንም።*

ከሊፋ አብዱላሂ ለአፄ ዮሐንስ የሚከተለውን ምላሽ ላከላቸው።

> *ይድረስ ለዮሐንስ*
>
> *የላከው ደብዳቤ ደርሶኝ ተረድቼዋለሁ ያቀረብከው የሰላም ጉዳይ እርቁ የሚወርደው ማተብህን በጥሰህ ሰላምታ የምትሰጠኝ እንደሆነ ነው። ሃይማቱን የምትቀበል ከሆነ አንድ ሆነናልና መልካም ወዳጅነት ሊኖረን ይችላል። ለዚህ ዝግጁ ካልሆንክ ግን የፈጣሪም የነቢይም ወዳጅ አይደለህምና አንተን ለመደምሰስ ግዴታ አለብኝ። ይህን ከማድረግም ሌላ አማራጭ የለኝም።*

የተጀመረው የወንድማማቾች ጦርነት አንዱ ሌላውን እስካላጠፋ ድረስ የማይበርድ መሆኑ እርግጥ ሆነ።

# ዘመቻ ዮሐንስ

አፄ ዮሐንስ ገላባትን፣ ብሎም ኦምድሩማንንና ካርቱንምን በመያዝ የድርቡሽ መንግሥት ለመገርሰስ ዝግጅት መጀመራቸው ሱዳን ውስጥ ጭምጭምታ ተሰማ፡፡ ዮሐንስ በዋነኞቹ የጦር መሪዎች በእነ ራስ አርአያ ድምፁ፣ ራስ ሚካኤል (መሐመድ አሊ)፣ ራስ ኃይለ ማርያም ጉግሳ፣ ራስ አሉላ፣ ሰልሐ ሻንቆ እና ሌሎችም ታላላቅ የጦር አዛገሮች የሚቀንቀሳቀሱ ክፍለ ሠራዊቶችን በመምራት በቅድሚያ ገላባትን ለመዝመት ዝግጅት በማድረግ ላይ መሆናቸው ወሬው ተናኘ፡፡ 20,000 ፈረሰኞችን ጨምሮ ከ150,000 በላይ ሠራዊት መርተው አፄ ዮሐንስ ገላባትን ለማጥቃት ዕቅድ እንዳነደፉ የድርቡሽ ሰላዮች ዝርዝር መረጃውን ለድርቡሽ መሪ አቀረቡ፡፡

ዜናው ገዝፎ በተሰራጨ መጠን ገላባትም ሆነ ኦምድሩማን በሽብርና በጭንቅ ይናጡ ጀመር፡፡ ለእኛ በማህዲው ምርኮ ሥር ላለነው የውጭ ዜጎች ግን የኢትዮጵያ ሠራዊት መምጣት ታላቅ የተስፋ ብርሃንን ፈነጠቀልን፡፡

የገላባቱ ምሽግ ዋና አዛዥ ሸክ ዘኪ ጡማል በመምጣት ላይ ያለውን ጠላት ከምሽግ ውስጥ ሆኖ መዋጋት ወይስ ገና ከመንገድ ላይ መቁረጥ የትኛው እንደሚሻል አማካሪዎቹን አወያየ፡፡ ካለምንም ማወላወል ምሽጋቸውን ማጠናከር አማራጭ ያሌለው ዘዴ መሆኑ እርግጥ ነበር፡፡ እንደማዕበል የሚነጉደውን የኢትዮጵያ ሠራዊት ከምሽግ ወጥቶ መመከት የማይታሰብም የማይሞከርም ነበር፡፡

ዮሐንስን ለመግጠም የተመደበው የዘኪ ጡማል ጦር 80,000 ደርሷል፡፡ ከቁጥሩ በላይ ጦሩ ምሽጉን አጥብቆ በመያዝ የመጣበትን ጦር ለመመከት ቁርጠኛ ነበር፡፡ አዋጅ ነጋሪዎች በገጠር በከተማው እየዞረ ሱዳናዊ ሁሉ የዕለት ተግባሩን ትቶ ጠብመንጃውን አንግቶ፣ ጎራዴውን ታጥቆ አገሩን እንዲከላከል የመሪአቸውን ትዕዛዝ አሰሙ፡፡ በሌላ በኩል የኢትዮጵያ መንግሥት የዘመቻ ዝግጅት ከተነገረው በላይ ተጠናክሮ መቀጠሉን የድርቡሽ ወታደራዊ ምንጮች ገለፁ፡፡ እነዚህ ወደ ኢትዮጵያ በመግባት መረጃዎችን ያሰባሰቡ የነበሩ ሰላዮች የኢትዮጵያን ሠራዊት እንቅስቃሴ በሚከተለው መልክ አቀረቡት፡፡

"የሀበሻ ሠራዊት እንደሰማይ ከዋክብት እንደባህር አሸዋ ህልቆ መስፈርት የለውም፡፡ ሠራዊቱ ሲርመሰመስ ለዓይን እይታ የሚታክት፣ መጨረሻው ከአድማስ ባሻገር የሆነ፣ የዘመቻው ንቅናቄ በሚያስነሳው ምድራዊ ደመና ፀሐይን ያጠቆረ አስፈሪ ኃይል ነው፡፡"

ይህ ደማቅ ወታደራዊ ዘገባ የድርቡሾች ዋና ከተማ አምድሩማንን ከወዲህ ወዲያ በሽብር አናወጣት፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ሱዳን በሀበሻ እንደምትጠፋ፣ የንጉሡ ፈረስም ኮቴው በፈሰሰው ደም ተውጦ፣ እንደ ወሬ ነጋሪ ከጥፋት በተረፈች አንዲት ዛፍ ጥግ ታስሮ እንደሚታይ እንደ ትንቢት የሚነገረው አፈ-ታሪክ ጊዜው መድረሱና ትንቢት የተነገረለት የሀበሻ ንጉሥ ዮሐንስ እንደሆነ ትንቢት ተናጋሪዎች አስረዱ፡፡

በ1881 ዓ.ም. ወርኀ የካቲት መጨረሻ ላይ ንጉሠ-ነገሥቱ ጎንደር ከተማን ለቅቀው በመውጣት ሕዝብን ለማጥፋት የተነሳውን ቁርጠኛ ጠላት ለመደምሰስ ሠራዊታቸውን በረድፍ በረድፍ አስከትለው ወደ ገላባት ተመሙ፡፡ እከተማዋ አቅራቢያ እንደደረሱ "እንደሌባ ተሽሎክሉኮ መጣ" እንዳትለኝ ለፊልሚያው ተነስቻለሁና ተነስ፣ ሲሉ ለድርቡሽ አዋጊና የጦር አዛዥ መልዕክት ሰደዱለት፡ ከኢትዮጵያ ሠራዊት ጋር

ከወንዶቹ ሌላ በርካታ ቁጥር ያላቸው ወይዛዝርት አብረው ተሰልፈዋል፡፡ እነዚህ ሴት ዘማቾች የትዳር ጓደኞቻቸውን፣ የእጮኞቻቸውን፣ የወንድሞቻቸውንና የአባቶቻቸውን የሞትና የመከራ ጽዋ ለመቅመስ ኑሮአቸውን በትነው፣ ጎጆአቸውን ዘግተው ወደ ጦር ሜዳ የዘመቱ ናቸው፡፡

በቅዳሜ መጋቢት 1 ቀን 1881 ዓ.ም. አፄ ዮሐንስ የገላባትን ምሽግ ማጥቃት ጀመሩ ሠራዊታቸው መሪውን እየተከተለ ከምሽጉ ውስጥ በፉከራና በቀረርቶ እየዘለለ ገባ፡፡ ከጦር አውድማው የሚነሳው አቧራ አውሎ ነፋሱ ብድግ ሲያደርገው እሽክርክሪት እየሠራ በውጊያው መሀል ሰይጣናዊ ጥፈራውን አቀለጠው፡፡ ከወዲያም ከወዲህ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ለዘመን ፍጻሜ የሚዋደቁት ወታደሮች አንዱ ሌላውን ለመለየት በማይቻልበት ሁኔታ የሞትና የመከራው ብዛትና ጥልቀት የቀኑን ብርሃን ጽልመት አለበሰው፡፡ ንጉሠ-ነገሥት ዮሐንስ ጦርነቱ መሀል ገብተው ሲዋጉ ያየው የኢትዮጵያ ወታደር መንፈሱ በአንዳች ወኔ እየተፈነቀለ ግስጋሴውን ቀጠለ፡፡ የድርቡሾች ጠንካራ ምሽግ መላላትና መሳሳት ጀመረ፡፡

ከድርቡሾች ሰይፍና የጥይት አረር ይልቅ የኢትዮጵያን ጦር የከበደው ነገር በአገር ምድሩ የበቀለው እሾህማ ጥቅጥቅ የቀላ ግራር ነበር፡፡ ለድርቡሾች ተደራቢ ምሽግ ሆነላቸው፡፡ ሀበሾቹ ግራሩን ግራ ቀኝ ረግጠው እየዘለሉ፣ አንዳንድ ጊዜም እያቃጠሉ ወደ ዋናው የድርቡሽ ማዘዣ ጣቢያ ዘልቀው ለመግባት ሲዋጉ የድርቡሽ ሠራዊት አጋጣሚውን በመጠቀም ጥይቱን አርከፈከፈው፡፡ በዚህ የትንቅንቅ ሰዓት ነበር ከማህዲ ሰፈር አምልጠው ለኢትዮጵያ ሠራዊት እጃቸውን የሰጡ ትኩሪሮች (ደቡብ ሱዳናውያን) ጠቃሚ መረጃ የሰጡት፡፡ በድርቡሾች የጦር ሰፈር "ደካማው የውጊያ ግንባር" ዋዲ አሊ ራሱ በሚያዋጋበት ግንባር በኩል መሆኑን ምርኮኞቹ ተናገሩ፡፡ የኢትዮጵያ ሠራዊት አብዛኛው ኃይሉን ወደ ሸክ ዋድ አሊ የጦር ግንባር በማዞርና በመረባረብ ለመጨረሻው ድል የሞት ሽረት ውጊያውን አፋፋመ፡፡

## ዋይታና እልልታ

በሁሉቱም ወገን ከተከፈለ ከባድ የሕይወት መስዋዕትነት በኋላ የኢትዮጵያ ሠራዊት እንደ ውቅያኖስ ማዕበል እያስገመገመ ከፊት ለፊቱ የቆመውን ሁሉ እየደመሰሰ የደርቡሾችን ወታደራዊ እምብርት ዘልቆ በመግባት የበላይነቱን ተቀዳጀ፡፡ ድልን ጨብጦ በመገስገስ ላይ የነበረውን ኃይል በተመለከቱ ጊዜ ከኋላ ሆነው ግፋ በለው እያሉ እልል ሲሉ የዋሉት በሺዎች የሚቆጠሩ ድርቡሽ ሴቶች ልብ የሚነካ እዬዬና ዋይታ ያሰሙ ጀመር፡፡ የኢትዮጵያ ጦር አሁንም ማጥቃቱን በመቀተልና ያገኘውን ድል በማጠናከር የድርቡሾችን ምሽግ ሙሉ በሙሉ ተቆጣጠረ፡፡ ይህ ግስጋሴ ሀበሾችን ወደ ፍፁም ድል በር የሚያደርሳው ወሳኝ እርምጃ ነበር፡፡

ጦርነቱ ጠላትና ወገን የማይለይበት፣ ዋይታና እልልታ የተደበላለቀበት፣ የሀም ልጆች በጥፋታቸው እንዲጠፉ ከላይ የታዘዘላቸውን የመከራ ፍርድ የሚፈፀምበት የዘመን ፍጻሜ ይመስል ነበር፡፡ የገላባት (መተማ) ጦርነት ከዚያም ከዚህም የሀም ዘሮች እንደ ቅጠል ቢረግፉም ድል ፊቷን ወደ ዮሐንስ ማዞሯ አጠራጣሪ አልነበረም፡፡ ሀበሾች የድርቡሽን የትጥቅና የስንቅ ማከፋፈያ ማዕከልን ተቆጣጠሩ፡፡ የጦር አዛዡ አቡ አንጋ ጦርነቱን ይመራ የነበረው ከዚሁ ሠፈር ሆኖ ነበርና የዮሐንስ ወታደሮች የማዘዣ ጣቢያው መደምሰስን ተከትሎ የድርቡሾችን የሬሳና የቁስለኛ ክምር በማገላበጥ የራሱን የአቡ አንጋን አስከሬን ለማግኘት ፍለጋ ጀመሩ፡፡ ጎንደር በእሳት ስትጋይ ቃጠሎው እስኪቆም ድረስ ከዳር ቆሞ ሲመለከት

የነበረው አቡ አንጋ ከተቻለ ከነሕይወቱ ካልሆነም ሬሳውን በማንደድ የጎንደርን ጥፋት ለመበቀል ነበር የኢትዮጵያውያኑ ምኞት። አቡ አንጋ ግን ሸሽቶ አምልጧል።

ከማዘገር ጣቢያቸው ሙሉ በሙሉ መደምሰስና ትጥቅና ስንቃቸው በኢትዮጵያ ሠራዊት መማረክ በኋላ የድርቡሾች ወኔ ሟሸሸ። የድርቡሽ ጦር በእጁ የያዘው ጥይትና ሌላ አስፈላጊ የውጊያ መሣሪያ አልቆ መዋጋት በማይችልበት ደረጃ ላይ በመድረሱ የዮሐንስ ዘማች ኃይል አሸናፊነት እርግጥ ሆነ።

## የንጉሥ ራስ

ድርቡሾች ተሸንፈው እግሬ እውጭኝ እያሉ በሚሸሹበት ሰዓት ንጉሠ-ነገሥት በአንዲት ጥይት ተመትተው መውደቃቸው በኢትዮጵያውያን ሰፈር ተሰማ። ወሬው እንደ እሳት ቋያ እየተቀጣጠለ ጦሩን በጠቅላላ ከወዲያ ወዲያ እያገላበጠ ያንገበግበውና ግራ ያጋባው ጀመር። በድርቡሽ ቆራጥነት ያልተፈቱት ሀበሾች በድል አፋፍ ላይ ቆመው የድርቡሽን ሽሽት አሻግረው በሚመለከቱበት ሰዓት በንጉሠ-ነገሥታቸው መመታት ድንጋጤ ጥርጣሬና ተስፋ መቁረጥ ወረራቸው። ከድል በኋላ በንጉሠ -ነገሥቱ ላይ በተተኮሰችው ጥይት ምክንያት የኢትዮጵያውያኑ ሠፈር ተስፋ መቁረጥና ትካዜ ገባበት። ካለ መሪ ካለ አስተባባሪ የቀረው የኢትዮጵያ ሠራዊት ያፈሰውን የድል አዝመራ ሳይሰበስብ ፊቱን ወደአገሩ በማዞር ጉዞ ጀመረ። ድል ፊቷን ወደ ኢትዮጵያውያን ብታዞርም እቅፍ ድግፍ አድርገው ስላልተንከባከቧት ድርቡሽን መረጠች። የአፄ ዮሐንስ በጥይት መመታትና የሠራዊታቸውም ማፈግፈግ የሰሙት ድርቡሾች ነገሩ እውነት አልመስል እያላቸው ከየተበተኑበት እየተሰበሰቡ ወደተደመሰሰው ምሽጋቸው መመለስ ጀመሩ። እዚያ ሲደርሱ የሰሙት ሁሉ እውነት መሆኑን አረጋገጡ።

የኃይለኛው የጦር መሪ የዋድ አሊ ክፍለ ሠራዊት ሳይቀር አብዛኛው የድርቡሽ ጦር ከበርካታ የጦር አለቆች ጋር ሙሉ በሙሉ የተደመሰሰ ቢሆንም በአፄ ዮሐንስ መመታትና በሠራዊታቸውም መበተን የመዋጋት ፍላጎታቸው እንደገና ያንሠራራው ማህዲስቶች የለቀቁትን ምሽግ እንደገና በመቆጣጠር በየቦታው የወደቀውን ሙትና ቁስለኛ ኢትዮጵያዊ አንገት እየቆረጡ ለድል ማብሰሪያነት በግመሎቻቸው እየጫኑ ወደ አምድሩማን ላኩ። የገላባቱን ጦርነት ኦምድሩማን ላይ ሆኖ በጭንቅ ሲከታተል የነበረው የማህዲስቶቹ ጌታ ኸሊፋ አብዱላሂ የሀበሾች ራስ ቅሎች ተደርድረው ሲቀርቡለት አይቶ ኸሊድ አህመድን እጅግ አድርጎ አመሰገነው።

የማህዲስቶች መንፈስ ግን ገና ሙሉ በሙሉ አልተረጋጋም። ሀበሾች ኃይላቸውን አደራጅተው በሁለተኛው ቀን አዲስ ውጊያ ይጀምራሉ ብለው ጠብቀውም ነበር። ቀናት አለፉ ድርቡሾች ተገረሙ። ከኢትዮጵያውያን በኩል የጥይት ድምፅ ፈጽሞ አልተሰማም። የድርቡሽ ሰላዮች የኢትዮጵያውያንን ኮቴ ተከታትለው እንዳረጋገጡት ደግሞ ሠራዊቱ በጠቅላላ በሀዘንና በትካዜ ጉዞውን ወደ ተከሴ አቅጣጫ መቀጠሉን ተረዱ። መረጃው የደረሰው የድርቡሽ ክፍለ ሠራዊት አዛዥ ዘኪ ጡማል ተበታትኖ አገሩ ለመግባት በየአቅጣጫው ይጓዝ የነበረውን የአፄ ዮሐንስ ጦር ተከታትሎ ለመግጠም ወሰነ። የድርቡሽ ኃይል በመጋቢት 11 ቀን 1981 ዓ.ም. ተከዜ ወንዝ ላይ ደረሰ። በወንዙ ዳርቻ የሰፈረውን ገና አሁንም ከፍተኛ ቁጥር ያለውን ዘማች ጦር ከፊት ለፊት ገጠመው። ውጊያው ተጧጧፈ። በእልህና በቁጭት አዲስ ውጊያ የከፈተው የድርቡሽ ኃይል በመሪው ድንገተኛ ሞት ምክንያት ሰማይ ፈርሶበት ካለ መሪ

የቀረውን ሠራቲት ያጠቃ ጀመር። የድርቡሽን የሞት ሽረት ጥቃት መመከት ያልቻለው የኢትዮጵያ ሠራዊት ከፍተኛ ጉዳት ደረሰበት የተከዜ ወንዝን ለመሻገር በየአቅጣጫው ተበተነ። ድርቡሾች ኢትዮጵያውያን የለቀቁትን ሠፈር ተቆጣጠሩ። ዓይኖቻቸውን የሳባው ነገር በሰም የታሸገ ረዥም ሳጥን ነበር፤ ውድ ዕቃ የያዘ መሰሏቸው ከፍተው ለማየት ጓጉ። ሳጥኑ የአንድ ረዝም ሰው አስከሬን የተኛበት መሆኑን ያወቁት ከፍተው ከተመለከቱ በኋላ ነው። የተራ ሰው አለመሆኑን በቀላሉ ተገነዘቡ። የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት አስከሬን በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ እዚያ ቦታ ይገኛል ብሎ ለመገመት ግን ከማንም ሰው አስተሳሰብ ውጭ ነው። እውነታው ግን የሆነው ነበር ዚኪ ነገሩን በመጀመሪያ በጥርጣሬ ዓይን ነበር የተመለከተው በውጊያው የተማረኩት ቁስለኛ ኢትዮጵያውያን ተጠየቁ፡፡ በሳጥኑ ውስጥ ያለው አስከሬን የአፄ ዮሐንስ መሆኑን አረጋገጡለት። የዮሐንስ አንገት በሰይፍ ተቆርጦ ለድል ማብሰሪያነት በግመል ተጭኖ ወደ ኦምድማን ተላከ።

## የንጉሥ ራስ በአደባባይ

የአፄ ዮሐንስን አንገት የተላከላት ኦምድሩማን ከተማ በሆታና በእልልታ ተናወጠች። የማህዲስቶቹ መሪ ኸሊፋ አብዱላሂ በመላዋ ሱዳን የድል እንቢልታ እንዲነፋ፣ ከበሮ እንዲደለቅ፣ ተኩሱ እንዲቀልጥና ጎራዴ እንዲያፏጭ አዘዘ። ጎን ለጎን መጠነ ሰፊ ፍሊጋ እንዲካሄድ ተወሰነ። ከዮሐንስ በተጨማሪ የሌሎች ታላላቅ የሀበሻ ምድር የጦር ጀግኖች አንገት ተቀልቶ እንደሆነ ለድሉ ተጨማሪ ድምቀት ተፈለገ። የራስ አሉላ፣ የራስ ኃይለማርያም፣ የራስ ሳልሕ ሻንቆ አንገትም እንዲሁ ተቆርጦ በግመል ኦምድሩማን ገብቷል እየተባለ በስፋት ተወራ። ቀስ በቀስ ግን ወሬው ወሬ ሆኖ ቀረ።

ያም ሆኖ የኸሊፋ አብዱላሂ የደስታ ስሜት ዳርቻ ሊገኝለት አልቻለም። በድርቡሾች ቁጥጥር ሥር ገብተን ነፃነት ለተነፈግነው ለእኛ ለአውሮጳውን ቁም እስረኞች ግን የጭለማ ወቅት ነበር፤ ነፃነታችን በኢትዮጵያውያን እጅ መሆኑን እናውቅ ነበርና።

የተሰየፈው የዮሐንስ አንገት በግመል ላይ ተጭኖ በሕዝቡ ሆታና እልልታ ታጅቦ በኦምድሩማን ከተማ አደባባዮች እንዲዞር ተደረገ። "ይህን ያየ ይቀጣ" ተባለ "የሱዳኖች ሆታና ጭፈራ ቅጥ አጣ" ኸሊፋ አብዱላሂ በድል ሰከረ።

## ምርኮ

በምርኮ ከተገኙት የንጉሠ-ነገሥቱ ንብረቶች መካከል ሦስት ጊዜ ተለብዶ በብራና ላይ ዘርዘር ተደርጎ በአማርኛ ቋንቋ የተጻፈ አንደባራቂና አስገራሚ ወንጌል ይገኝበታል። "Crosidi Paris" የሚል ጽሑፍ ያረፈበት የቀናትና የወራት መቁጠሪያ ያለው የወርቅ ሰዓት፣ የጦር ሜዳ መነጽር እና ከንግሥት ቪክቶሪያ ለንጉሠ-ነገሥቱ የተላከ ደብዳቤ ትኩረትን የሚቡ ነበሩ፡ ከንግሥቲቱ የተላከውን ደብዳቤ ለማንበብ ዕድል አግኝቼአለሁ የሚለተለውን ቁም ነገር ያዘለ ነው።

*ይድረስ ለግርማዊ ንጉሠ-ነገሥት ዘኢትዮጵያ ዮሐንስ ራብዓይ። ስለ እርስዎና ስለመላ ቤተሰብዎ ሰላምና ጤና እንደምን ሆነዋል። ታላቋ ብሪታንያ የግብጽ የበላይ አስተዳዳሪ በመሆንዋ የኢትዮጵያ የቅርብ ጎረቤት ልትሆን በቅታለች። ይህ መልካም አጋጣሚ ከግርማዊነትዎ ጋር የዘላቂውን የሰላምና የወዳጅነት ግንኙነት በበለጠ ለማጠናከር ይጠቅመናል የሚል ከልብ የመነጨ እምነት አለኝ።*

*በተረፈ ለግርማዊነትዎ የተሟላ ጤንነት፣ ሰላምና ረዥም እድሜ እምኛለሁ።*

ከንግሥት ቪክቶሪያ የተላከው የወዳጅነትና የመልካም ምኞች መልዕክት የአገሪቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የ[illegible]ሎርድ ሶልሰበሪ ፊርማ አርፎበት ይገኛል።

ከዚህ በተጨማሪ የንጉሠ-ነገሥቱ የዘመቻ ድንኳን፣ እንዲሁም በልዩ ልዩ ቀላመት የደመቁ መስቀሎች ተመልክቼአለሁ።

## <u>የዕድል ድል</u>

የአፄ ዮሐንስ ራስ አንገት በኦምድሩማን አደባባይ ለትንግርት ቀርቦ እንደበቃ የዕለቱ ዕለት በቆዳ ተለብዶ ወደ ደንጎላ (ዳርፉር ግዛት) ከዚያም አልፎ እስከ ግብጽ ድንበር ድረስ በግመል ተጭኖ እንዲወሰድ ኸሊፋ አብዱላሂ አዘዘ። ዓላማው ግልጽ ነው። በማህዲዝም ላይ የተነሱ ሱዳናውያንም ሆኑ እንግሊዞችና ግብጾች "ይቅርና እናንተ የዮሐንስ ዕጣ ፈንታም የኸው ነው" የሚል ማስጠንቀቂያ ለመስጠት ነው።

የኸሊፋ አሸናፊነት የበላይነትና ማን አለብኝነት ሰማይ ጥግ ደረሰ። የማህዲስም ተከታዮች ፈንጠዝያ እየበረደ ሲሄድ በከተማው ስዚዚር ካዩኒቸው ዘግናኝ ነገሮች መሀል የተሰየፉ የሰው ልጆች ራስ ቅሎች ፀጉር እስኪገፈፍ ድረስ በየጉድጓዱ ተከምረው እንዲበሰብሱ መደረጋቸው ነበር። ከድርቡሽ ተቃዋሚዎች መሀል የእነ ሱልጣን ዩሱፍ፣ አቡ ገማዥ፣ ሱልጣን ኢሳና የሌሎች ሱዳናውያን እንደዚሁም የበርካታ ኢትጵያውያን ራስ ቅሎች በየጉድጓዱ ተጥለው አላፊ አግዳሚው ሁሉ አፍና አፍንጫውን ከድኖ እንጨት ይሰድባቸዋል። ራቅ ካሉ አካባቢዎች ተይዘው ከነቆባቸው አንገት አንገታቸው የተሰየፉ ካህናትና መነኮሳት በአንድ ጉድጓድ ውስጥ ተጥለው አይቻለሁ። ሁሌም በዚያ መንገድ በወጣሁ በወረደሁ ቁጥር ወንደም በወንድሙ ላይ እንዲህ እንደምን ሊጨካከን እንደቻለ መልስ እያጣሁለት መንፈሴ ይረበሽ ነበር።

ይህ ትንግርታዊ ትርኢት የማህዲዝም ኃይል ከየት እስከየት እንደደረሰ በማሳያነት የቀረበ ቢሆንም በጦር ሜዳው ውሎ ላይ እንድቅጠል የረገፉትን በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ሱዳናውያንን ነፍስ የሚመልስ አልነበረም። የደረሰው ያ እልቂት ያየ ተመልካች ፈጣሪ ሱዳን ላይ ያወረደው መዓት እንጂ በሰው ኃይል የተፈጸመ ነው ብሎ ለመቀበል ይከብደዋል።

የሆነ ሆኖ ለጊዜውም ቢሆን ኸሊፋ አብዱላሂ የምድሪቱ ጌታ ሆኖ መታየቱ አልቀረም። እርሱ ባላቀደው መንገድ እንዲህ ዓይነት ያልተጠበቀ ድል መቀዳጀቱ ህልምና እውነት እየተቀላቀለበት "እንዴት ሊሆን ቻለ?" እያለ መደመሙ አልቀረም።

በድርቡሽ በኩል የገላባትን (የመተማን) ጦርነት የመራው ዘኪ. ጡማል እንደነበር ከፍ ሲል ገልጸናል፡፡ ዘኪ. የኸሊፋ አበዱላሂ የቅርብ ዘመድ ነው፡፡ ቢሆንም በጦርነቱ ስለደረሰበት ሽንፈት፣ ከፍተኛ ኪሣራና ስለረገፈው ስፍር ቁጥር የሌለው ተዋጊ ዝርዝር ዘገባ ለመሪው ማቅረብ አልፈለገም፡፡ ህዝቡም በዮሐንስ አንገት መሰየፍ ከተሰማው መጠን የሌለው የድርቡሽ ደስታ የተነሳ ስለሠራዊቱ ጉዳትና ኪሣራ ለማወቅም ሆነ ለመጠየቅ ጊዜ አልነበረውም፡፡ ከዚህ በላይ መሪአቸውን በሚያሞካሹና ስለአሸናፊነቱ በሚመጻደቁ ሰዎች የተከበበው ኸሊፋ ስለጦር ሜዳው እውነተኛ ውሎ ሲነገረው የሚችል አልተገኘም፡፡ ቢገኝም እንኳ በወታደራዊ ኃይሉ ምድርን ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ ያንቀጠቀጠውን የዮሐንስን አንገቱን ቆርጦ በቆዳ ሰፍቶ መተረቻ በሚያደርግበት ወቅት ስለማህዲዝም ውድቀትና ኪሣራ የሚሰማበት ጆሮ አልነበረውም፡፡

## ዋናው ጠላት

ሱዳን በማህዲስቶች አክራሪነትና ጦረኝነት የተነሳ የገባችበት ቀውስ ለአንድ ዓመት ያህል ሕዝቦችዋ በረሃብ እንዲሰቃዩ አደረገ፡፡ የድርቡሾች መሪ ግን በአጋጣሚ ያገኘውን ድል ገና አጣጥሞ ስላላበቃና ሥልጣን የማደላደሉ ሥራ ላይ በመጠመዱ የሱዳን ዋና ጠላት ከረሃብ በላይ ሌላ ሊኖር እንደማይችል ገና አልተገነዘበውም፡፡ ኸሊፋ ስለአገኘው የበላይነተና አዲሱን የአክራሪነት እምነት ይበልጥ ስለሚያስፋፋበት መንገድ ማሰብ እንጂ አፍጥጦ ስለመጣው የረሃብ ጠላት የሚጨነቅበት ፋታ አልነበረውም፡፡

ሆኖም መከራ ሁሉንም አስተማሪ ነውና ረሃብ ሕዝቡን እየፈጀው ሲሄድ ኸሊፋም ስሜቱ እየበረደ፣ ፊቱንም ወደ ሕዝቡ ችግር እያዞረ መጣ፡፡ ከጦርነቱ ፍጻሜ በኂላ በሁለቱ አገሮች ሕዝቦች የገባው ድርቅና ረሃብ ሁለቱንም ሕዝቦች ለሰላምና ለወዳጅነት ያቀራርብ ጀመር፡፡ የቆየ የንግድ ግንኙነታቸውን ቀስ በቀስ እንደገና ማደስ ጀመሩ፡፡ የዚህም አገር (የሱዳን) እንዲሁም የዚያ አገር (የኢትዮጵያ) ነጋዴዎች ንግድ ልውውጣቸውን እንደ ድሮው ባይሆንም አለፍ አለፍ እያሉ አካሄዱ፡፡

በነጋዴዎች መካከል የንግድ መስመሮች ቢከፈቱም ድርቡሾች ግን ዛሬም ቢሆን በማህዲስቶች ዘመቻ፣ በረሃብና በርስ በርስ የሥልጣን ሽሚያ የተዳከመችውን ኢትዮጵያ በተከታታይ ከማጥቃት አልቦዘኑም፡፡ ኢትዮጵያውያን በርስ በርሱ ቁርቁስ ውስጥ በመግባታቸው ኃይላቸውን እንደገና አደራጅተው በረሃብና በጦርነት የተደከመውን የድርቡሽን ኃይል እንደገና ለመውጋት አልቻሉም፡፡

የሱዳንን ምድር ቀስፎ የያዘው ረሃብ እየከፋና እየሰፋ ሄደ፡፡ ኢትዮጵያ ጋር ፍፁም ሰላምን መሥርቶ የሁለቱም አገራት ሕዝቦች የሚበጃቸውን ማድረግ እንጂ ቂም በቀል ከውድመት በቀር ምንም ፋይዳ የሌለው መሆኑ ግልጽ ሆነ፡፡

እንደ እነ ሼክ አብዱራህማን፣ ዋዲ እና አቢ ደገል የመሳሰሉ ሩቅ አሳቢ የሱዳን አባቶች የችግር ሁሉ ብቸኛ መፍትሄ ንግድ እንጂ ጦርነት አለመሆኑን በየአደባባይ አስተማሩ፡፡ ሀበሻና ሱዳን የፈረሰውን የሰላም ድልድይ እንደገና ገንብተው እነሆ እስከዛሬ ባልተቋረጠ ሰላማዊ ጉርብትና አብረው ይኖራሉ፡፡